# የኤምባሲ በሮችና ዴሞክራሲ

ብዕር ከአቃቂ

በየኤምባሲው ደጅ የሚጠኑ፣ ወረፋ በመጠበቅ ላይ ያሉና እንደ እድል ሆኖ የአምባሳደሮች ፊት የሚያዩ ፖለቲከኞች እየበዙ መምጣታቸውን ኤምባሲዎች አካባቢ የሚሠራው ጓደኛየ በነገረኝ ማግስት የግል ጋዜጦችም ይህን እንደ ርእሰ ወሬ ይዘው ያዦጎደጉዱት ጀምረዋል።

በተለይም የአንድነት ፓርቲ መሪዎች ከአገር ቤት ትላልቅ ርዕሰ ጉዳዮች ይልቅ የተለመዱ ጭንጋፍ ጉዳዮች አጠረቃቅመው በተለያዩ ኤምባሲዎች ደጅ መጥናት ከጀመሩ የሰነባበቱ ቢሆንም ከሰሞኑ እንደ ትልቅ ድል ተቆጥሮ በፓርቲው ልሳን ከዚያም ይህንን ተከትለው በሚያስተጋቡ የግል ጋዜጦች የተወራላቸው የእንግሊዝ አምባሳደርን አግኝተው ማነጋገራቸውን በሚመለከት ነው።

የአንድነት መሪዎች አምባሳደሩን አነጋግረናል-መንገዶች ፈር ይይዛሉ ብለው ደረታቸውን ነፍተው ለልሳናቸው ሹክ አሉ። ምንም እንኳ ይህ ነው የሚባል ተከታይ እያጡ በውስጣቸው ያለን ጥቃቅን የሃሳብ ልዩነት ለመፍታት የሚፈራሩት ተቃዋሚ የፖለቲካ ፓርቲዎች ለተራረፈው አባላቸውም ቢሆን ትልቅ የድል ብስራት ብለው አቀበሉት-የእንግሊዝን አምባሳደር ማነጋገርን።

ለመሆኑ የዴሞክራሲ ጫወታ ሜዳ የት ነው ያለው? የጫወታው ዳኛስ ማነው? ህዝቡ አይደለምን፡፡ለነዚህ ጥያቄዎች ምላሹ ግልፅ ቢሆንም ህዝቡን እየሸሹ የኤምባሲ በር ድልን የአንድነት አመራሮች ሊነግሩን ይሞክራሉ፡፡ ሕዝብ ዘንድ ሲሆን ሥፍራ የማይሰጠው የጊዜ ጉዳይ ኤምባሲ ሲደረስ እንደትልቅ ጉዳይ ይቆጠራል፡፡ ደቂቃውን ሳይቀር አስልተው ያሰምሩበታል።

የአንድነት አመራሮች የ45 ደቂቃ ቆይታ ከአምባሳደሩ ጋር። ፓ! እንዴት ላብ ጠብ የሚያደርግ ትግልና የትግል ውጤት ነው? እንዲህ አይነት በኤምባሲዎች ጫና የፖለቲካ ጉዳይ የማስፈፀም የዜሮ ድምር ፖለቲካ በኋላ ላይ የምመለስበት ሆኖ ለጊዜው በፓርቲውና በእንግሊዙ አምባሳደር መካከል የተካሄደውን ውይይትና የአምባሳደሩን አስተያየት ለማቅረብ ወደድኩ።

የአንድነት መሪዎች የዘወትር መዝሙር የሆነው የወይዘሪት ብርትኳን ሚዴቅሳ መታሰር የህግ የበላይነት ማስከበር መሆኑን ሽምጥጥ አድርገው በመካድ ነበር ለደጅ ጥናት ኤምባሲ በር ድረስ የሄዱት። የአንድነት አጀንዳና የአምባሳደሩ መልስ ግን የትየለሌ ሆኖ መገኘቱን የግል ጋዜጦቹ አስነብበውናል። ጥያቄ ብለው በዋናነት የወሰዱት የሃገሪቱ የዴሞክራሲ ተቋማት ከሆኑት መካከል ፍትህ የሚመለከታቸው ፍርድ ቤትና በፍትህ ሚኒስትር ስር ያሉ መሥሪያቤቶች ያስተላለፏቸውን ውሳኔዎች አምባሳደሩ እንዲያስቀይሩ የሚያመለክተውን ነበር።

አምባሳደሩ ዲፕሎማት ናቸውና የህግ የበላይነት ከተረጋገጠበት የወይዘሪት ብርትኳን ሚዴቅሳ ጉዳይ ዞር ብለው ለመሆኑ በምርጫ ጉዳይ ምን እያሰባችሁ ነው አሏቸው?

አከል አደረጉ የእንግሊዙ አምባሳደር “በ2002 ምርጫ ለመሳተፍ ጥረት ቢደረግ መልካም ነው” ብለው የምርጫ ሥርአት ውስጥ ገብቶ መስራትን የመሰለ የዴሞክራሲ ጨዋታ እንደሌለ ካደጉበትና የሰከነ ውድድር ከሚካሄድበት የእንግሊዝ ዴሞክራሲ ትምህርት ሰጥተዋቸው መመለሳቸውን ተረዳን- ከግል ጋዜጦቹ ዘገባ።

ከዘገባዎቹ እንደተረዳነው አምባሳደሩ ምክር ላይ ፓርቲው በምርጫ ስለመሳተፍና አለመሳተፍ የ97ቱን የሚመስል ፍንጭ ሰጥቶ እርፍ አለ።ያኔ ከአራት ዓመታት በፊት ለምርጫ ተሳትፎ “እየመጣን ነው አልደረስንም” ያሉትን አሁንም ለመድገም እደተዘጋጁ የሚገልፅ መልስ ሰጡ። በምርጫ 97 ያደረጉትም ይህንኑ ነበር። እስከ ድምፅ መስጫው እለት ልንሳተፍ እንችላለን አንችልም እያሉ ዥዋ ዥዌ እየሰሩ መዝለቃቸውን ማንም የሚረሳው ጉዳይ አይደለም።አሁንም ከጅምሩ ልንሳተፍ የምንችለው እገሌ ከተባበረን ነው የሚል መልስ ሰጡ።

ትብብር ምን ድረስ? ኳሱስ ማን ሜዳ ላይ ነው ያለው? የሚሉትን ጥያቄዎች እንይ። በምርጫ አሸንፎ ስልጣን የመያዝ ሳይሆን ሰለማዊውን የትግል ሂደት የሚበጠብጥ፤ ራሱን የምርጫውን ሂደት ለብጥብጥና አመፅ በመጠቀም ህገ መንግስታዊውን ሥርአት እንዳለ የመናድ የዜሮ ድምር ፖለቲካ በ97ቱ ምርጫ ወቅት በአማራጭነት ይዛችሁ እንደነበር የኢትዮጵያን መንግስትና ህዝብ ይቅርታ በጠየቃችሁበት ወቅት ነግራችሁናል። መንግስት ግማሽ መንገድ ሄዶ እንደተቀበላችህ ለማረጋገጥም ፍርድ ቤት የእድሜ ልክ እስራት ከወሰነባችሁ በኋላ የይቅርታ ህጉን ተከትሎ ጥያቄያችሁን አስተናገደው።ጥያቄያችሁን መቀበል ብቻ አይደለም በሰላማዊ የፖለቲካ እንቅስቃሴ ውስጥ እንድትሳተፉም ወስኖ ሜዳውን ሰጣችሁ። ከዚህ በላይ ግማሽ መንገድ ሄዶ መቀበል ምን አለ? ኳሱስ እናንተው እጅ አይደለም ያለው?

የመንግስትንና የህብረተሰቡን ትግስት የመፈታተኑ አባዜ አሁንም አልለቀቃችሁ ይሆናል የሚል ጥርጣሬ ስለሚያድርብን ነው እንደ ዜጋ እነዚህን ጥያቄዎች እያነሳን ያለነው። ለዚህም ነው ተቃዋሚዎቻችን ከኤምባሲ ደጅ ጥናትና የህግን የበላይነት ለማረጋገጥ ወደ ማረሚያ ቤት የወረዱ ሰዎችን የተመለከቱ - ዋነኛ ሳይሆኑ ጭፍጫፊ ጉዳዮች ላይ ከማተኮር ወጥተው ወደ ትክክለኛ፣ ሰላማዊና ዴሞክራሲያዊ ትግል የመግባት ሞራል፣ ብቃትና ዝግጁነት አላቸው ወይ የሚለውን እንደ ዜጋ የምናነሳው ። ገዥው ፓርቲ ስንት አባላት አሉት እያሉ ሚሊዮን ቁጥር ሲሰሙ እየደነበሩ ጭፍጫፊ ጉዳዮች ይዞ በየኤምባሲው ደጅ ከመጥናት ይልቅ ዴሞክራሲያዊና ሰላማዊ ውድድር መርጣችሁ መቼ ይሆን የምታሳውቁን?

<u>**ተመሳሳይ ላባ ያላቸው ...**</u>

ከላይ አንዱን ፓርቲ አንስቼ ተቃዋሚ እያልኩ ማጠቃለል የወደድኩት “ተመሳሳይ ላባ ያላቸው ወፎች አንድ ላይ ይበራሉ” የሚለውን የፈረንጆች አባባል የሚያመለክት አስተሳሰብ ሰሞኑን መድረክ ተብሎ የሚጠራው ስብስብ ከፍተኛ አመራር ውጭ ለሚገኙ ደጋፊዎቻቸው ያሉትን ስላስታወሰኝ ነው።እኝህ ሰው አንድ አስገራሚ ጥቅስ ብቅ አድርገዋል “**መርህ ያልገራው ፖለቲካ**” እንከተላለን የሚል። ፖሊሲ፣ አይድዮሎጂ፣ አማራጭ የአስተሳሰብ ልዩነት የሚባሉ ጉዳዮችና የዴሞክራሲ ነገር ልንሰማው የማንፈልግ፣ ልናውቀው የማንሻው፣ የማይገባን ነገር ነው አሉና የሻዕቢያ

መንግሥት መርህን እንዳለ ዘረገፉት። ለነገሩ ምክርና ምግብ ከቤት ነው እንዲሉ ቤታቸውም መካሪያቸውም ሻዕቢያ አይደል።

ይኸው ነው እንግዲህ በሃሳብና በአስተሳሰብ ልዩነት ላይ የተመሰረተ መቻቻል፣ ጥቅሞችን ማጣጣም፣ አመክንዮና የህግ የበላይነት የሚባሉ ነገሮች የማን ናቸው ብለው የሚጠይቁ የ21ኛው ክፍለ ዘመን ተቃዋሚዎች ኢትዮጵያ ውስጥ ብቅ ሲሉ ሊገርመን የሚችለው። አሃ! ልክ ነዋ በዚህ ጉዳይ ላይ እኮ እናንተ የላችሁበትም። ይልቁንም እናንተ የምትሉት በተቃዋሚዎች መካከል ያለን ልዩነት አትጠይቁ፣ ዝም ብላችሁ በቀደድነው በር ተጓዙ። ታዲያ እንዲህ ዓይነቱን ጉዳይ የ97ቱ ቅንጅትም ሲለን የነበረ፣ በኋላም ውጤቱ ሳያምር ስድስት ብጥስጣሽ ቅንጅት የፈጠረ አካሄድ መሆኑን ማንም የሚገነዘበው ነው።

ስለዚህ ለተቃዋሚዎች የሚነሳላቸው ጥያቄ አብራችሁ ስትበሩ ቁልቁል በምታዩት ሙዳ ሥጋ ላይ እንዴት ታርፉላቹህ? የሚል ነው። መልሱ እንደ መድረክ አመራሮች መርህ የማይገራው ፖለቲካ ከሆነ ደግሞ ውጤቱ የእልቂት መንገድ ለመሆን የሚቀነቀን አስተሳሰብ እንጂ ከዴሞክራሲ ጋር ለየቅል ነው። ይህን አስተሳሰብ ደግሞ ህብረተሰቡ አይቀበለውም። በመጨረሻ ተቃዋሚዎች ለሰላማዊና ዴሞክራሲያዊ ውድድር የሚሆን ወኔ፣ ችሎታ፣ አቅሙና ዝግጁነቱ አላችሁ ወይ? እንደ ዜጋ አሁንም ብንጠይቅም ሊኖራችሁ ግን ይገባል እንላለን።

ነገር ግን መርኅ አንሻም፣ በየኤምባሲው ደጅ መቀላወጣችንን አንተውም፣ የሚያዋጣን ይህና ከቻልንም አመፅ ነው የምትሉ ከሆነ ከዚህ በፊት በተግባር እንዳያችሁት የኢትዮጵያ ሕዝብ አንቅሮ ይተፋችኋል። አሃ! ልክ ነዋ። እፍኝ ሆናችሁ አይደል ሰልፍ የወጣችሁ? ስለዚህ ሰላማዊና የዴሞክራሲ መርሆዎች የሚጠይቋቸውን ጉዳዮች አንግባችሁ ወደ ጨዋታው ሜዳ ግቡ የዘወትር ምክሬ ነው። ሰላም!

---END---